ምድሩን እንዲለኩና ቦታዎችን ለጥፋት ምልክት እንዲያደርጉ መላእክት በፍጥነት ተልከዋል!

ትንቢት USAን አስመልክቶ በ ሳድሁ ሱንዳር ሴልቫሬጅ

Prophecy Concerning USA By Sadhu Sundar Selvaraj

ጁን 19 እና 20፥ 2015

በጁን 19፥ 2015 ከቀኑ 11:43 ላይ በኮስታ ሜሳ፥ ካሊፎርኒያ ውስጥ ስብሰባ እያደረግሁ ሳለ፥ ጌታ ኢየሱስ ጎበኘኝ። ሰገነቱን በሚመለከተው በተንሸራታቹ በር አጠገብ እርሱ ቆመና፥ "ና እና ከአጠገቤ ቁም።" አለ። ስለዚህ መጣሁና ከጌታ አጠገብ ቆምሁ። ከተማዋን እየተመለከትን ነበር። እርሱም:- "ወረቀት እንደሚቀደድ፥ ይህ ቦታ ለሁለት ይቀደዳል/ይከፈላል።" አለ። (እርሱ ይህ ቦታ ሲል፥ 'ካሊፎርኒያ' እንደሆነ በመንፈሴ አስተዋልሁ)። እኔም ለጌታ:- "ለምን? ጌታ ሆይ ለምን?" አልሁ። ከዚያም ጌታ:- "ምክንያቱም እርሷ የእኔን ምድር ትቀድዳለች/ትከፍላለች" አለ። ምድሩ እስራኤል እንደሆነ ተረዳሁ። ጌታ ቀጠለ፥ "እርሷ በእጇቿ ምድሬን ትቀድዳታለች፥ ከሕዝቤ ጋር ያደረገችውን ቃል ኪዳን ትቀድዳለች። ዩ ኤስ ኤ ከእስራኤል ጋር ያደረገቻቸውን ስምምነቶች(ውሎች) ሁሉ ትቀድዳለች። ስለዚህ፥ አስጠንቅቃት። ይህን አስመልክቶ የአሜሪካ ሕዝብን አስጠንቅቅ።"

"ጌታ ሆይ፥ ሕዝብህስ? ምድሩን የምታወድመው ከሆነ፥ ክርስቲያኖችስ?" ብዬ ጌታን ጠየቅሁት። "ከዚህ ቦታ(ማለትም ከካሊፎርኒያ) እንዲሸሹ ማስጠንቀቂያ ይሰጣቸዋል። ሎጥ እንደተጠበቀ እነርሱ ይጠበቃሉ። ለሰዶምና ገሞራ ፍርድ የማይቀር ነበር። ነገር ግን አብርሃም ስለጸለየ እና ሎጥም ደግሞ ጻድቅ ስለነበረ፥ የተበከለች እንዳትሆን ነፍሱን እርሱ ጠበቀ።" በማለት ጌታ ነገረኝ። እዚህ ጋር ሁለት ነገሮች አሉ። አንደኛው የምትጸልይ ቤተክርስቲያን፥ ሌላኛው ጻድቅ ሰው (THE REMNANT/ ቅሬታዎቹ) ነበረ። በዚያ ምክንያት፥ ሎጥ ተጠበቀ።

ምድሩን እንዲለኩና ቦታዎችን ለጥፋት ምልክት እንዲያደርጉ መላእክት በፍጥነት ተልከዋል።

በቀጣዩ ቀን፥ በጁን 20፥ 2015 በምሽት ሰዓት 12:45 ላይ፥ መጥቶ ከፊቴ የቆመ አንድ ኀያል መልአክ አየሁ። መልአኩ በእጁ ጥቅልል (scroll) ይዞአል፥ እርሱም ከጥቅልሉ ማንበብ ጀመረ፥ "እኚህ ሕዝብ (አሜሪካውያን)፥ ለጥፋት ተለይተዋል!" እኔም በድንጋጤ ነበርሁ! በዚያ ጊዜም በዩናይትድ እስቴትስ በሙሉ በብዙ ቦታዎች መላእክት አየሁ፥ እነርሱ ጥፋትን ለመፈጸም(execute) እየጠበቁ በሁሉም ቦታ ቆመው ነበር። በተለይም፥ ለበጣም ኃይለኛ ጥፋት ለከባድ መሬት መንቀጥቀጦች በተመረጡ በ3 የተለያዩ ቦታዎች ቆመው አየኋቸው! ቦታዎቹ የትኞቹ እንደሆኑ አላውቅም፥ ነገር ግን እነርሱ(መላእክቱ) ቆመው 3 ቦታዎችን ምልክት ሲያደርጉ አይቻቸዋለሁ። ከዚያ ይህ መልአክ ተመለከተኝና፥ "የሰው ልጅ ሆይ፥ እኚህ ሰዎች ከፉዎችና ግትር ናቸው።" ከነነዌዎችና ከሰዶምና ገሞራ የባሱ። አስጠንቅቃቸው። ጸሎትና ንስሐ ሊያድን ይችላል።" አለ።

**በስሜ የተጠሩት ሕዝቤ ሰውነታቸውን አዋርደው ቢጸልዩ፥ ፊቴንም ቢፈግሉ፥ ከክፉ መንገዳቸውም ቢመለሱ፥ በሰማይ ሆኜ እሰማለሁ፥ ኃጢአታቸውንም ይቅር እላለሁ፥ ምድራቸውንም እፈውሳለሁ።** (2ኛ ዜና መዋዕል 7:14)

## **ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና ዛሬ እስከ ለዘላለምም ያው ነው።**

ፓርት 1 እና ፓርት 2 ጠቅላላ መልእክቱን ለመስማት

ፓርት 1 https://www.youtube.com/watch?v=xTG-mcuLOyc

ፓርት 2 https://www.youtube.com/watch?v=Jx7v9fubXb8

# ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና ዛሬ እስከ ለዘላለምም ያው ነው።

ስም የሌለው፥ የማይታወቅ፥ ጌታውና አምላኩ በሆነ በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ጸንቶ የሚኖርና የሚታመን፥ ሊያደርግ የሚገባውን ያደረገ አንድ የማይጠቅም ባሪያ በመንፈስ ቅዱስ ተመርቶ ተረጎመው። ክብር ሁሉ፣ ኃይልም ብርታትና ጥበብም ውዳሴና ምስጋናም፣ ግርማና ሞገስም፣ ዝማሬና እልልታም ማዳንና ቅድስና ለቡሩክ መልካም ቅዱስ የእስራኤል አምላክ ለአባታችን ለእግዚአብሔር አብ ይሁን ለታረደው በጉም ለጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ለቡሩክ ቅዱስ መንፈሱም ብቻ ይሁን አሜን ሃሌ ሉያ። ማራናታ ጌታ ያሑሹዋ ሐማሺያክ የእግዚአብሔር ልጅ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ቶሎ ና አሜን!

http://www.baptizingfire.com , http://fireofgodservants.blogspot.com/ , http://www.thelordshour.com , http://www.choothomas.org , http://www.Jesusministries.org/ , http://www.angeltv.org , http://www.Billygraham.org , http://free.messianicbible.com/ , http://www.levitt.tv/ ,

http://www.divinerevelations.info/amharic , http://www.heavenvisit.com , http://www.tribulation-now.org , http://www.voe.org/ , http://www.sidroth.org , http://repentandpreparetheway.org/ , http://www.shekinahworship.com/ , http://www.theblazingholyfire.com/ , http://www.thelastreformation.com ,

http://www.bobjones.org/ , http://www.annarountree.com/ , http://www.beyondthephysicalrealm.com , http://www.shreveministries.org , http://www.blogtalkradio/tribulation-now , http://www.bullsere.kr/ http://www.blogtalkradio/thelordshour , http://www.blogtalkradio.com/discoveringthetruth

http://www.be4thefire.com/ , http://www.e-sword.net/ , http://www.blogtalkradio.com/coming-apocalypse , http://lamarzulli.net/